የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)
*Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

## መግለጫ

## በሃይማኖት ልዩነት የተነሳ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይጣላም

ጥር 2001 ዓም

ለአለፉት አስራ ስምንት ዓመታት ወያኔ በዘረጋው የውርደትና የመከራ አገዛዝ፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ በዘር፥ በቋንቋና በሃይማኖት ከፋፍሎ ለማጫረስ የተደረገው ሙከራና ዕኩይ ግፊት፥ በአርቆ አስተዋዩ ሕዝባችን እንደከሸፈ ታሪክ የመዘገበው ሃቅ ሆኗል፡፡ ይህም ክስተት የኢትዮጵያን ሕዝብ ታላቅነትና ታሪካዊነት በድጋሜ አረጋግጦለታል፡፡ ወያኔና ባዕዳን ጠላቶቻችንንም አሳፍሯል፡፡ ሀገራችንን በስልት ለማፈራረስ የተደረገውን ከንቱ ጥረት ሁሉ አክሽፎታል፡፡

በዘመናት፥ የአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች፥ የኦቶማን ዓፄያዊ ግዛትና ሌሎች ሀገር አስፋፊዎች እየተፈራረቁ በመምጣት፥ በሃይማኖት ስም ይኽችን ውድ ሀገራችንን ለማጥፋት ያደረጓቸውን ጥቃቶች ሁሉ በየጊዜው የነበረው ቀደምት ትውልድ መስዋዕትነትን እየከፈለ እንዳመጣጣቸው እያሳፈረ በመመለስ፥ ለተተኪው ትውልድ እያስረከበ አልፏል፡፡ ይኽ የዛሬው ትውልድም በተራው፥ በወቅቱ በተነሱት የውስጥ ከሃዲያንና ባዕዳን የበላይ ጠባቂዎቻቸው ትብብር ሀገራችንን በብሄርና በቋንቋ ለመከፋፈል የተደረገውን ሙከራ ሁሉ በአብዛኛው እንዳከሰመዉ የዘመናዊው የሀገራችን ታሪክ በኩራት መዝግቦታል፡፡ የወያኔንም መርዘኛ ዕቅድ ድምጥማጡን አጥፍቶታል፡፡ በዘርና በቋንቋ ልዩነት ምክንያት ሀገሪቱን ለመከፋፈልና ለማጥፋት ያደረገው ዕቅድ እንዳልተሳካለት ተገንዝቦ፥ ዛሬ ይህ መርዘኛ ዕባብ ወቅቱን እየጠበቀ ቆዳውን በመሸልቀቅ፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ በሃይማኖት ለመከፋፈል ሰሞኑን አንድ የመጨረሻ ሙከራ ለማድረግ በመቅበዝበዝ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህ ሳምንት በተከበረው የጥምቀት በዓል ላይ የወያኔና የባዕዳን ቅጥረኞች በዘመናት ተከባብሮና ተስማምቶ በአንድነት የኖረውን ሕዝብ በሃይማኖት ለማበጣበጥ ሙከራ እንዳደረጉ የአደባባይ ምሥጥር ሆኗል፡፡ በዚህ ዕኩይ ድርጊት በድሬዳዋና በጎንደር ከተሞች ምዕመናን ላይ በተደረገው ሽብር ቁጥራቸው በትክክል ያልተመዘገበ ምዕመናን ህይወታቸውን እንዳጡ በመገናኛ ብዙኃን ተገልጿል፡፡ በርካታ ንፁኃን ዜጎችም መቁሰላቸው ተረጋግጧል ፡፡ ይህ የሰው ህይወት መጥፋትና መቁሰል በሚያስፈራ ደረጃ ተስፋፍቶ ወደ ከፍተኛ የደም መፋሰስ ባለመድረሱ የታሪኩ ባለቤት የሆነው እስላሙና ክርስቲያኑ ምዕመን እንደገና ታላቅነቱን አስመስክሯል ለማለት ይቻላል፡፡ ታላቅ አክብሮት የተመላበት ምስጋናም ሊቀርብለት ይገባል ፡፡ የወያኔም ተንኮል ግቡን

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

እንዳይመታ ሆኗል። ያማ ባይሆን ኖሮ፥ ሀገራችን በሃይማኖት ብጥብጥ ምክንያት የደም ጎርፍ ትለቀለቃት ነበር። ያ ግን አልሆነም። ወደፊትም የሚከሰት አይሆንም ብሎ በዕርግጠኝነት መናገር እንደሚቻል በሕዝባችን አስተዋይነትና ታላቅነት አንጠራጠርም ። ምክንያቱም፥ ክርስቲያኑ ዝክሩን እስላሙም ሰደቃውን በጋራ እያከበረ፥ አብሮ እየበላ እየጠጣ የኖረ ሕዝብ ስለሆነ ነው።

ኢሕአፓ የወያኔን ድርጊት አጥብቆ እየኮነነ በዚህ የጥምቀት በዓል ላይ በጠፋው የንፁሃን ዜጎች ሕይወት ጥልቅ ሀዘኑን ይገልፃል ። ለሟቾቹ ቤተሰቦችም የሀዘን ማፅናኛውን ያስተላልፋል። ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነቱንና ኅብረቱን በማጠንከር፥ ዘለዓለማዊ ታላቅነቱን በድጋሜ በማስመስከር ወያኔንና ባዕዳን ጠላቶቹን እንዲያሳፍር ብሔራዊ ጥሪዉን በድጋሜ ያቀርባል። ሕዝብን በሃይማኖት ሊከፋፍሉ የሚጥሩትን የውስጥና የውጭ ሀይሎችንም በጥብቅ ያወግዛል።

ኢትዮጵያ ሀገራችን ለዘለዓለም ትኖራለች!

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ